# ነፃ ሚዲያ?

ለመንደርደሪያ ያክል ይሄንን አርእስት የሰጠሁበትን ምክንያት ለአንባቢያን ላካፍል እወዳለሁ፣ ይህንን አርእስት የመረጥኩበት የባለቤቴ የናቷ ታናሽ ወንድም የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንደማንኛውም አገር ወዳድ ሁሉ ይከታተላል በየ ድሕረገፆች ላይ የሚወጡትን የሐገራችንን ወቅታዊ ዜናዎች ከማንም በበለጠ አንድም ሳያመልጠው የግለሰቦችንም አስተያየት ጨምሮ ምጥጥ ካደረገ በኋላ ሁሌም ማሳረጊያው "እዬ እነኚህ የ(Basement Media) ዎች" ይላል ፣ ሁሌም በሚሰጣቸው ትችቶችና አቀራረቦች እገረማለሁ ፣ ባብዛኛው እስማማለሁ አንዳንዴም ግር ሲለኝ ያይና ሁኔታውን በርጋታ ሰፋ ባለ መንገድና ምሳሌዎችን በማከልና በመተንተን ሲያስረዳኝ ያልተስማማሁባቸው አንዳንድ ነጥቦች ላይም ከስምምነት እንደርሳለን ያም ማለት ግን ሙሉ ለሙሉ እንስማማለን ማለት ሳይሆን ባይሆን ሰማንያ በመቶው ጉዳይ ላይ እንግባባለን ሆኖም ግን ሁሌም አንድ የማንግባባበት ነገር ቢኖር በደንብ የተማረና ሰለሐገሩም ሆነ ስለውጪው ዓለም ታሪክና የፖለቲካ አደረጃጀት ጥሩ ግንዛቤ እያለው በሐገሩ ጉዳይ ላይ ተግባራዊ የሆነ ተሳትፎ ባለማድረጉ ሁሌም ቅር እሰኛለሁ። ስለወቅቱ ትግል ያለውን ትምህርታዊና ገንቢ የሆነ አስተያየት እንዲጽፍና ከተቻለም በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እንዲሳተፍ ስጠይቀው አንተ የኢትዮጵያ ፓለቲከኞችንና የኢትዮጵያን ሚዲያዎች አታውቃቸውም በማለት ለምን ተሳታፊ መሆን እንዳልፈለገ የሚሰጣቸው ነጥቦች አሉት በሱ እይታ እንደምክንያት የሚሰጣቸው አጥጋቢ ቢሆኑም አገርን ጉዳይ በተመለከተ ግን እምብዛም ለኔ አጥጋቢ ሆኖ አላገኘሁትም ። ሆኖም ግን አመለካከቱን አከብርለታለሁ ። ሁሌም ግን ስለሱ ተሳታፊ አለመሆን ሳስብ ኢትዮጵያ እንዴት ያለ ትልቅ ጭንቅላት ለሐገሩ ብዙ ማበርከትና ለውጥም ለማምጣት የሚችል ሰው አለግልጋሎት ቀረ በማለት በጣም አዝናለሁ ።

ስለሱ ያን ያክል ካልኩ በኋላ ወደ ዋናው ቁም ነገር ልመለስ ፣ ባለፉት ጥቂት ቀናት "መይሳው" በሚል የብእር ስም አንድ ጸሀፊ "ያልገባን ምኑ ነው?" እና "የትግላችን መዳከም ፣ የወያኔ መጠናከር" በተሰኙ ሁለት ርእሶች ጸሐፊው ስህተት የመሰላቸውን በትችት መልክ ለአንባቢያን ሊጠቁሙ ሞክረዋል ፣ በማከልም በአንደኛው ጽሑፋቸው አንባቢያንን አንዳንድ ድሕረ ገፆች ምን ያክሉ የግለሰቦችን አስተያየትና አመለካከት (Professional) መልክ ያስተናግዱ እንደሆነና (Criticism)ን ምን ያክል ለመቀበል ፍቃደኝነትን ያሳያሉ በማለት በጽሑፋቸው ላይ ጥርጣሬ በተሞላው አቀራረብ "ያልገባን ምኑ ነው?" በተሰኘችው ጽሁፋቸው ላይ ታዋቂ ለሆኑት ድሕረ ግፆችም በሙሉ ጽሁፋቸውን መላካቸውን በመጠቆም አንባቢያን ትዝብት እንዲወስዱ አሳስበው ነበር ፣ በሰጡንም ጥቆማ መሰረት እኔም ታዋቂ ሊሆኑ ይችላሉ ያልኳቸውን ድሕረ ገፆች በሙሉ አስሼ ጽሑፋቸውን ያገኘሁት በጥቂቶች ላይ ብቻ ነበር ፣ የባለቤቴ አጎትም የ( Basement Media) ያለበት ምክንያት አሁን ገባኝ ። በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር ታዋቂ ከሚባሉት ድሕረ ገፆች አንዱ የሆነው Addis Voice "የትግላችን መዳከም ፣ የወያኔ መጠናከር" በሚል እርእስ የወጣውን ያቶ መይሳውን ጽሑፍ ከሌሎች ድሕረ ገፆች ዘግየት ብሎ ከሶስት ቀን በኋላ በድሕረ ገጹ ላይ ለ 24 ሰዓት ካስቀመጠው በኋላ መልሶ አንስቷታል ፣ እንደኔ ጥርጣሬ ከሆነ መጀመሪያውንም ጽሁፉን የድሕረ ገጹ አዘጋጅ ሳያነብ ነበር ያወጣው ወይንም ጽሑፉን የተመለከቱና ትችቱ እኛ ላይ ነው የሚሉ

ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች ተፅእኖ አሳድረውበታል በየትኛውም መልኩ ቢሆን ድሕረ ገጹ አዘጋጅ ወገንተኛነትን ያንጸባርቃሉ ማለት ነው።

በርግጥም አብዛኛዎቹ የድሕረ ገጽ አዘጋጆች እንደ BBC ወይንም Reuters ባለ million dollar industry ብሎም በ ethics የታነጹ professional ጋዜጠኞች ሳይሆኑ (Self Proclaimed) ጋዜጠኞች እንዲያውም የግል ስራ ያላቸውና ጋዜጠኝነቱ በትርፍ ሰዓታቸው የሚያካሂዱ እንደሆነ ካብዛኛዎቹ የተደመጠ እውነታ ነው፣ የራሳቸው የሆነ አጀንዳ ያላቸው ወገናዊነትን አንጸባራቂ ግለሰቦች እንጂ የጋዜጠኝነት ተግባሩ ሲያልፍም እንደማይነካቸው ለመረዳትም አያዳግትም ፣ በመሆኑም የባለቤቱ አጎት የሰጣቸው ስም በቅጡ ይገልጻቸዋል ለማለት እደፍራለሁ ። እዚህ ላይ Addis Voice እንደ ለምሳሌነት ተጠቀሰ እንጂ ሁሎችም ማለት ባልችልም እንኳ አብዛኛዎቹ ወገንተኛ ለመሆናቸው አያጠያይቅም ፣ አቶ መይሳው ድምጻቸውን ማሰማት ባለመቻላቸው ጥልቅ ሀዘን ቢሰማኝም ልረዳቸው ባለመቻሌ አዝናለሁ። እንግዲህ ነጻ ሚዲያ ማለት እንዴት ነው? ነጻ በድሕረ ገጽ አዘጋጆች እይታ? ወይንም በወገኑት ድርጅት እይታ? ታዲያ የምንቃወመው ወያኔስ የሚያደርገው ይህንኑ አይደል ፣ ልዩነቱ የቱ ላይ ነው? በዚህ አይነት አሰራር እየተጓዝን ነው አገር ነጻ የምናወጣውና ወያኔን የምናወግዘው? Media ታፈነ እያልን ስሞታ እያሰማን እንዴት እኛው አፋኝ እንሆናለን? በእውነት ከሆነ አቶ መይሳው ያሉት የኛን ሚዲያ ተብዬዎች ጥሩ አድርጎ ስለሚገልጸን ላነሳው እወዳለሁ “ ባለዛርና ቃሊቻ እንዴት አድርጎ ነው ወንጌል ሊሰብክ የሚችለው” ያሉት አባባል ቀላል አይደለምና አባባሉን ትኩረት በመስጠት ከስህተታችን ብንታረምና ሌሎች የሚፈጽሙብንንና የምናወግዘውን ተግባር እኛም በአስተሳሰብ የማይመስሉንን censure በማድረግ ድምጻቸው እንዳይሰማ በማፈን ተግባር ከተሰማራን በኔ አመለካከት የምንታገለው መልስ ዜናዊን ፣ በለገሰ ዜናዊ ለመተካት እንዳይሆን ያሳጋኛል። እኔም እንዳቶ መይሳው ላሉት ድሕረ ገጾች በሙሉ በመላክ እድሌን እንደምሞክር ከማንም አልሸሽግም ። ልቦናውንና ቅንነቱን ይስጠን እላለሁ ።

ታከለ ከሰሜን አሜሪካ

እናሸንፋለን!!